# አይቢፕሮፌን (Ibuprofen)

## የመድሃኒት ስም ጀነሪክ፡- አይቢፕሮፌን

## አይቢፕሮፌን ብራንድ ስሞች፡- አድቪል(Advil) ሞትሪን(Motrin)

**ምድብ፡-** ስቴሮይድ ነክ ያልሆነ አንቲ ኢንፍላማቶሪ መድሃኒት (Non-Steroidal Anti-Inflammatory Drugs (NSAIDs))

## አይቢፕሮፌን ለምን ህመም ይወሰዳል?

አይቢፕሮፌን ለቀላል ህመሞች ማስታገሻ ሊወሰድ ይችላል። ለምሳሌ፡-

- ቁርጥማት
- አንጓ ብግነት(አርተራይተስ)
- የወር አበባ ህመሞች
- ትኩሳት ለማስታገስ
- ራስምታት
- የጥርስ ህመም
- ጉንፋን

## እንዴት ነው የሚሰራው?

ይህ መድሃኒት የሰውነት መቆጣትን(inflammation) በመቀነስ እና ከህመም ስሜት ጋር የተያያዙ የተወሰኑ ኬሚካሎች እንዲቀንሱ በማድረግ ህመምን ይቀንሳል ወይም ያስታግሳል።

## አይቢፕሮፌን በምን መልኩ ተመርቶ ይታሸጋል?

በፈሳሽ መልክ የሚወሰድ

በአፍ የሚዋጥ ክኒን

## አይቢፕሮፌን መውሰድ የሌለባቸው ሰዎች

1. ከዚህ በፊት ለአይቢፕሮፌን ወይም ለአስፕሪን የሰውነት መቆጣት(አለርጂ ያሳዩ ሰዎች) የአይቢፕሮፌን አለርጂ ምልክቶች የሚያሳክክ ሽፍታ፣ የፊት ማበጥ፣ ለመተንፈስ መቸገር፣ የቆዳ መቅላት፣ የቆዳ ውሃ መያዝ እና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ።
2. እርጉዝ ሴቶች ወይም ለመጸነስ ሃሳብ ያላቸው ሴቶች።
3. የሚከተሉትን መድሃኒቶች የሚወስዱ ሰዎች
    - የደም ማቅጠኛ (anticoagulants) ለምሳሌ ወርፈሪን(warfarin)
    - ስቴሮይድ(steroid) መድሃኒት የሚወስዱ። የስቴሮይድ መድሃኒት ምሳሌ ሜድሮል(Medrol) ነው።
    - አስፕሪን(Aspirin) የሚወስዱ ሰዎች።
4. በየእለቱ የአልኮል መጠጥ የሚወስዱ ሰዎች።
5. እንዲሁም የሚከተሉት ህመሞች ያለባቸው ሰዎች ያለሀኪም ፍቃድ አይቦፕሮፌን መውሰድ የለባቸውም

- አስም
- የልብ በሽታ
- የጉበት በሽታ
- ከፍተኛ ደም ግፊት
- ከደምስር ጋር የተየያዘ በሽታ(ለምሳሌ ስትሮክ)
- የኩላሊት በሽታ
- የጨጓራ ህመም
- ከዚህ በፊት በጨጓራ መቁሰል ወይም መድማት ያጋጠማቸው ሰዎች

## የአይቢፕሮፌን ትክክለኛ አወሳሰድ

ለቀላል ህመም ወይም ትኩሳት ለማስታገስ

- አንድ የሁለት መቶ ሚሊግራም(200 mg) ክኒን ይውሰዱ። ህመም ወይም ትኩሳት ካልታገሰ ከአራት እስከስድስት ሰአት ባለው ግዜ ውስጥ ደግመው መውሰድ ይችላሉ።
- አንድ የሁለት መቶ ሚሊግራም ክኒን ህመምዎን የማያስታግስ ከሆነ ሁለት ክኒን መውሰድ ይቻላል።
- ያለዶክተር ትእዛዝ በሀያአራት ሰአት ግዜ ውስጥ ከስድስት ኪኒን በላይ አይውሰዱ። ህመም ወይም ትኩሳት የማይቀንስ ከሆነ ሀኪምዎን ያማክሩ።

ይህን መድሃኒት ከምግብ ጋር ወይም ከወተት ጋር ይውሰዱ።

ለረጅም ግዜ አይቢፕሮፌን መውሰድ ለጨጓራ እና ለልብ ህመሞች ሊያጋልጥ ይችላል። ስለዚህ ለቀላል ህመሞች አይቢፕሮፌን ሲወስዱ ትንሹን መጠን ለአጭር ግዜ ብቻ ይውሰዱ።

## በዚህ መድሃኒት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮች

ይህ መድሃኒት የሚወስዱ አንዳንድ ሰዎች የሆድ ህመም (የጨጓራ ህመም፣ ማቅለሽለሽ፣ ማስመለስ፣ የሆድ ድርቀት፣ የሆድ መወጠር ስሜት፣ እና ጋዝ) ሊሰማቸው ይችላል። ይህን ለመከላከል ሁሌ መድሃኒቱን ከምግብ ጋር መውሰድ ይመከራል። በተጨማሪ በተቻለ መጠን ለአጭር ግዜ እና ትንሹን መጠን መውሰድ ጥሩ ነው። እንዲሁም የራስ ምታት፣ ሽፍታ፣ ጆሮ ላይ ጭው የሚል ድምጽ መሰማት፣ ራስ ማዞር እንዲሁም የምግብ ፍላጎት መቀነስ ሊከሰት ይችላል።

## መድሃኒቱ መቀመጥ ያለበት ቦታ

መድሃኒትዎን ሙቀት እና ቅዝቃዜ የማይበዛበት  ደረቅ ቦታ ያስቀምጡ። መድሃኒትን መታጠቢያ ቤት ማስቀመጥ አግባብ  አይደለም። ህጻናት እና የቤት እንስሳት የማይደርሱበት ቦታ ያስቀምጡ።

## ከፍተኛ ጥንቃቄ (FDA blackbox)

አይቢፕሮፌንን ጨምሮ ሁሉም ስቴሮይድ ነክ ያልሆኑ አንቲ ኢንፍላማቶሪ መድሃኒቶች ለልብ እና ደምስር በሽታዎች ሊያጋልጡ ይችላሉ። እነዚህ የልብ እና ደምስር በሽታዎች የደም መጓጎል ድንገተኛ የልብ ህመም እና ስትሮክን ያጠቃልላሉ።

እነዚህ ህመሞች ከዚህ በፊት ያጋጠመው ሰው ወይም ለእነዚህ በሽታዎች የሚያጋልጥ ተጨማሪ ህመም ወይም የቤተሰብ ታሪክ ያለበት ሰው አይቢፕሮፌን ሆነ በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙ መድሃኒቶችን ያለሀኪም ትእዛዝ መውሰድ የለበትም።

አይቢፕሮፌን እና ተመሳሳይ መድሃኒቶች ለጨጓራ እና ለአንጀት ህመም፣ መቁሰል(ulceration)፣ እና መድማት(bleeding)፣ አልፎም ለመቀደድ(perforation) ሊያጋልጥ ይችላል። እድሜያቸው የገፋ (ከ65 አመት እድሜ በላይ) ለዚህ የተጋለጡ ናቸው።

**ማጣቀሻ**
Ibuprofen Tablets [package insert]. Glasgow, KY 42141: Ameal Pharmaceuticals Corp.; 2014.
Motrin®Ibuprofen Tablets [package insert]. NY, NY 10017: Division of Pfizer Inc,.; 2007.
**ቀን:** 07/23/20